BBC LEARNING ENGLISH

# Essential English Conversation

## Shopping for clothes

## Size and Colour

*This is not a word-for-word transcript*

**ዘሩባቤል**
ጤና ይስጥልን። ማንኛውም የእንግሊዝኛ ተማሪ ሊያውቃቸው የሚገቡ የቋንቋ መሰረታዊያንን ወደሚያቀርበው Essential English Conversation እንኳን በደህና መጡ። ዘሩባቤል እባላለሁ። በዚህ ክፍል ገበያ ሲወጡ ስለሚጠቀሟቸው የተለያዩ መጠኖችና ቀለማት ይማራሉ።
ሁለቱ ሰዎች ሱቅ ውስጥ ሲያወሩ ያዳምጡ።

***Shop assistant***
*Can I help you?*

***Dan***
*Yes, do you have these shoes in size 9?*

***Shop assistant***
*No, but we have them in size 8 and 10.*

**ዘሩባቤል**
ይህ አስቸጋሪ ቢሆንብዎት ብዙም ጭንቀት አይግባዎት፤ ውይይቱን ከፋፍለን እንዲለማመዱት እናግዝዎታለን።
በመጀመሪያ ባለሱቁ 'Can I help you?' ሲል ለዳን ጥያቄ አቅርቧል።

*Can I help you?*

**ዘሩባቤል**
በመቀጠል ዳን 'Yes, do you have these shoes in size 9?' በማለት ጠይቋል። 'Do you have these in….?' የሚለውን ጥያቄ በሱቁ ውስጥ የምንፈልገው መጠን ወይም ቀለም መኖሩን ለመጠየቅ እንተቀምበታለን። ስለ አንድ እቃ ስንጠይቅ 'this' እንጠቀማለን። ብዙ ነገሮች ሲሆኑ ግን 'these' እንጠቀማለን። ስለዚህ ሱቁ ውስጥ ባለ ጥቁር ቀለም 8 ቁጥር መጠን ያለው ጫማ ለመጠየቅ እንደዚህ እንላለን።

*Do you have these shoes in black?*

*Do you have these in size 8?*

**ዘሩባቤል**
አሁን ያዳምጡና ደግመው ይበሉ!

*Yes, do you have these shoes in size 9?*


© British Broadcasting Corporation 2018

**ዘሩባቤል**
በመጨረሻም ባለሱቁ ‘No, but we have them in size 8 and 10.’ ብሏል። ያዳምጡና ደግመው ይበሉ።

*No, but we have them in size 8 and 10.*

**ዘሩባቤል**
በጣም ጥሩ! አሁን የሰዎቹን ንግግር በማዳመጥ እርሶ ካሉት ጋር ያመሳክሩ።

*Can I help you?*

*Yes, do you have these trousers in black?*

*No, but we have them in brown.*

*Can I help you?*

*Yes, do you have these sunglasses in white?*

*No, but we have them in silver.*

**ዘሩባቤል**
እሺ! በድጋሚ እንሞክር። የእንግሊዝኛ ንግሮቹን ያዳምጡና በድጋሚ ይበሏቸው። እያንዳንዱን ንግግር ሁለት ጊዜ ይሰማሉ።

*Can I help you?*
*Can I help you?*

*Yes, do you have these shoes in size 9?*
*Yes, do you have these shoes in size 9?*

*No, but we have them in size 8 and 10.*
*No, but we have them in size 8 and 10.*

**ዘሩባቤል**
በጣም ጥሩ! አሁን ደግሞ ምን ያህል እንደሚያስታውሱ እንፈትሽ። አረፍተ ነገሮቹን በአማርኛ ያዳምጡና በእንግሊዝኛ ይበሏቸው።

*ምን ልርዳዎት?*
*Can I help you?*

*አዎ! እንዚህ ጫማዎች በ9 ቁጥር አለዎት?*
*Yes, do you have these shoes in size 9?*

*አይ! በ8 እና 10 ቁጥር ግን አለን።*
*No, but we have them in size 8 and 10.*


© British Broadcasting Corporation 2018

**ዘሩባቤል**
ግሩም! አሁን እቃ ለመግዛት ሲወጡ መጠንና ቀለም እንዴት እንደሚጠይቁ አውቀዋል። እስቲ ከባለ ሱቁ ጋር ይለማመዱ። ባለሱቁ 8 ቁጥር ካልሲ ያለው እንደሆነ ይጠይቁት።

*Can I help you?*
*No, but we have them in size 8.*

**ዘሩባቤል**
ጥሩ! አሁን የእርሶ መልስ ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ ሙሉውን ንግግር ያዳምጡ።

***Shop assistant***
*Can I help you?*

***Dan***
*Yes, do you have these shoes in size 9?*

***Shop assistant***
*No, but we have them in size 8 and 10.*

**ዘሩባቤል**
በጣም ጥሩ! አሁን ወደ ሱቅ ሄደው የሚፈልጉትን መጠንና ቀለም መጠየቅ ችለዋል። የተማሩትን መለማመድ አይዘንጉ። ጓደኛ ይፈልጉና 'Do you have this/ these in….?' በማለት ልምምድ ያድርጉ። ለተጨማሪ የዕለት ተዕለት እንግሊዝኛ በሚቀጥለው ዝግጅታችን ይጠብቁን። Bye!


© British Broadcasting Corporation 2018